


የህግ ባለሙያ ባልሆነ ሰው ዓይን ሲታይ፥ በምንኖርበት አገር አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሲከሰስ፥ በመጀመሪያ ጥፋተኛ መሆኑንና አለመሆኑን ራሱ ተጠይቆ መልስ ይሰጣል። ጥፋተኛ ነኝ ካለ፥ ለጥፋቱ ተስማሚ የሆነ ቅጣት በህጉ መሰረት እንዲቀበል ይደረጋል። ጥፋተኛ አይደለሁም ካለ ግን ከዳኛው በተጨማሪ 12 ሰዎች ያሉበት ሸንጎ (ጁሪ) በጥንቃቄ ተመርጦ ይሰየማል። ጉዳዩ በአቃቤ ህግ ከሳሽነት ይጀመራል። አቃቤ ህግ ምስክሮቹን ይጠራል። ምስክሮቹ አቃቤ ህጉ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ከመለሱ በሁዋላ በተለምዶ መስቀልኛ ጥያቄ የምንላቸውን ጥያቄዎች በተከላካይ ጠበቃ በኩል ይቀርባሉ።

የተከላካይ ጠበቃ፥ የሚሟገትለትን ሰው አጥፊ አለመሆን ለማረጋገጥ በተለያየ ጥያቄ ያቃቤ ህጉን ምስክሮች ያጣድፋቸዋል። ምስክርነታቸው ውስጥ የማይጣጣሙ ነገሮች ካሉ፥ ሸንጎው ፍርዱን በሚሰጥበት ጊዜ ሊወስንባቸው ከሚችልባቸው ነጥቦች መካከል እንዲሆኑ በማስታወሻ ይዞ ያስቀምጣቸዋል። አቃቤ ህጉ የሚያቀርባቸውን ምስክሮች ከጨረሰ በኋላ ምስክሮች የማቅረቡ ስራ ወደ ተከላካይ ጠበቃው ይዞራል።

ተከላካዩ ጠበቃ የሚሟገትለትን ሰው ወንጀለኛ አለመሆን በምስክርነታቸው ያረጋግጡልኛል ብሎ የሚተማመንባቸውን ሰዎች ይጠራል። በሸንጎው ፊት ጥያቄዎች ያቀርብላቸዋል። እያንዳንዱ ምስክር በተከላካይ ምስክር ተጠይቆ ሲያበቃ፥ አቃቤ ህጉ ደግሞ የራሱን መስቀልኛ ጥያቄ መጠየቅ ይጀምራል። በዚህ ሁሉ ውስጥ የሸንጎው አባላት ፍርድን ለመስጠት ይጠቅመናል የሚሉትን ማስታወሻ ባለማቋረጥ እየያዙ የተከሳሹን በደለኛነት ወይም ንጽሕና ለመፍረድ ጉዳዩን በከፍተኛ ኃላፊነት ይከታተላሉ።

በተጨማሪም የክሱን ጉዳይ በሚመለከት አቃቤ ህጉም ሆነ ተከላካዩ ካስፈለገ፥ የየራሳቸው ከፍተኛ ባለሙያ (ኤክስፐርት) ምስክሮች ያዘጋጃሉ። መርሳት የሌለብን ሌላ ዋና ነገር፥ ገና ክሱ ከመመሰረቱ በፊት የወረዳው (እንደ ክሱ አይነት) የፌዴራሉ አቃቤ ህግ መስሪያ ቤት አጥፊ ያልሆነን ሰው ላለመክሰስ በሚያደርገው ጥንቃቄ አያሌ ምርመራዎች በማድረግ በስህተት የተጠረጠሩ ሰዎችን ከመካከል አውጥቶ፥ ለአጥፊነቱ በቂ ማስረጃ አለኝ ያለውን ሰው ብቻ ለፍርድ ያቀርባል። በተጨማሪ የፖሊስ ላቦራቶርም በጥንቃቄ የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች ከተከሳሹና ከክሱ ጋር የሚገናኙ ለመሆናቸው በቂ ምርመራ አድርጎ ትክክለኛው ተከሳሽ ይህ ሰው ነው ብሎ ለወረዳው ወይም ለፌዴራሉ አቃቤ ህግ ከሰጠው ሪፖርት የተነሳ አጥፊ ነው የተባለው ሰው ይከሰሳል።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ፍትህ እንዳይጓደል አቃቤ ህጉ የተከሳሹን በደለኛነት ኢምንት ጥርጣሬ በሌለበት ማረጋገጫ ማስመከር ሲኖርበት ተከላካይ ጠበቃ ግን ተከሳሹ አጥፊ አለመሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ እንኳን የለበትም። የተከሳሹን አጥፊነት ማመን የማያስችል መጠነኛ ጥርጣሬ መፍጠር ከቻለ ተከሳሽ በነጻ ይለቀቃል። አይፈረድበትም። የፋይል አቀራረብ፣ ማስረጃ አሰባሰብና ሌሎችም ያሰራር መንገዶች በምንም አይነት ሁኔታ የተከሳሹን መብት በሚነካ መንገድ ተሰርተው ከነበረ ተከሳሹ በነጻ ይለቀቃል። እነዚህ ሁሉ መጥለያዎች የተደረጉት 12 የሸንጎ አባላትና በችሎት ላይ የተሰየመው ዳኛ ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ስለሚታመንና ምናልባት የተከሰሰው ሰው አጥፊ ሳይሆን ሊፈረድበት ይችላል በሚል ስጋት የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ናቸው።

የሚገርመው ነገር ግን፥ መንግስት ይህን ያህል ጥንቃቄ ቢያደርግም፥ በቀርቡ የዲ.ኤን.ኤ. ሳይንስ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ የተነሳ፥ አጥፍተዋል ተብለው ተፈርዶባቸው ለረጅም ዘመናት በእስር ቤት የማቀቁ ሰዎች ተፈቱ። ያለ ጥፋታቸው የሞት ፍርድ የተቀበሉ ሰዎችም እንዳሉ ጋዜጠኞች ዘገቡ። በአጭር አነጋገር የሰው ልጅ ለመፍረድ አሁንም ብቃት እንደሌለው ተረጋገጠ። ፍርድን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የላቦራቶሩ ምርመራ፣ የመርማሪዎች መስቀልኛ ጥያቄ፣ የተበዳዮች አቤቱታ፣ የምስክሮች ቃል፣ የጠበቃዎች ችሎታ ሊያወጣው የማይችለውን እውነት እግዚአብሔር ያውቀዋል። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ብቻ ፍርድን ያውቃል የምንለው። ምክንያቱም እርሱ የማንም ማስረጃ አያስፈልገውም፣ የሸንጎ ምክር አያስፈልገውም። ረዳትም አያስፈልገውም። ምክንያቱም እርሱ ሳያይና ሳያውቅ የሚሆንና የሚደረግ ምንም ነገር የለም። በሌላ በኩል ግን ሰዎች ሊገኝ የሚችለውን ማስረጃ ሁሉ ሰብስበው ሊያዩ የማይችሉት ነገር ደግሞ ስለሚኖር ይሳሳታሉ። ከዚያ የተነሳ ለፍርድ ብቁ አይደሉም።

ሁለት አይነት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን (በአማኞች ኅብረት) ውስጥ ችግርን ሲፈጥሩ ይታያሉ። እነርሱም የመጀመሪያዎቹ የዲያብሎስን ስራ በመሻማት (ራእይ 12፥10) በሌሎች አማኞች ላይ ክስ ሲመሰርቱ የሚውሉ ሲሆኑ፤ ሁለተኞቹ ደግሞ ስለሚሰሙት ክስ በቂ እውቀት እንደሌላቸው ባለማወቅ የእግዚአብሔርን ስራ ካልሰራን የሚሉ በሌሎች ሲፈርዱ የሚውሉ ናቸው። ሁለቱም ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ጠንቅ ከመሆናቸውም በላይ የራሳቸውን መንፈሳዊ ሕይወት አቀጭጨው የኅብረቶችን ግስጋሴ የሚያዳክሙ ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል እነዚህን ሰዎች በሚመለከት የማያወላዳ መመሪያ ይሰጣል።

*"ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና መሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንደነዚህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ። "* (ሮሜ 16፥17-18)

*"መለያየትን የሚያነሳ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ከገሰጽከው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ።"* (ቲቶ 3፥10)

*"እነዚህ የሚለያዩ ስጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው።"* (ይሁዳ 1፥19)

ክሱን ለዲያብሎስ ፍርድን ደግሞ ሁሉን ማየት ለሚችለው ለእግዚአብሔር ትተን፥ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር በፍቅር እንመላለስ። ጌታ እንዳለ፥ ሕግና ነቢያት በዚህ ተሰቅለዋል። (ማቴዎስ 22፥36-40) እግዚአብሔር ይርዳን።

© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS